# ጽርሐ አርያም

"አ እግዚአ አድኅኖ" መዝ ፻፲፯፥፳፭

"አቤቱ እባክህ አሁን አድን" መዝ ፻፲፯፥፳፭

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ርእሰ አድባራት ጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል
2601 Minnehaha Ave, Minneapolis, MN 55406 Tel: 612-913-7000

ሚያዚያ ፳፻፰ ዓ.ም/ቅጽ ፩/ቁጥር ፩ | ወርኃዊ ጋዜጣ | April 2016/Volume 1/Issue 1

## ፈትታችሁ አምጡልኝ



የተወደዳችሁ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የርእሰ አድባራት ጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ምእመናን አባቶች፣ እናቶች፣ ወንድሞች እና እኅቶች እንኳን በቤተ ክርስቲያናችን በታላቅ ድምቀት ለሚከበረውና ከታላላቅ በዓላትም አንዱ ለሆነው ለበዓለ ሆሣዕና አደረሳችሁ። የዚህ ታላቅ በዓል ምንነት ታሪክ በአራቱ ወንጌላውያን ተጽፎ ይገኛል። ይኸም በዓል የሚከበረው ጌታችን በአህያይቱና በውርንጭላዋ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም የገባበትን ዕለት በማሰብ ነው። (ማቴ. ፳፩፡፩-፲፯) በዚህም የነቢዩ ዘካርያስ ትንቢት ፍጻሜን አግኝቷል። (ዘካ.፱፡፱) ከወንጌሉ ታሪክ እንደምናነበውም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን **"በፊታችሁ ወዳለች ከተማ ሄዳችሁ የታሰረች አህያ ከነውርንጭላዋ ታገኛላችሁ ፈትታችሁ አምጡልኝ ማንም ስለዚህ ነገር ቢጠይቃችሁ ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ።"** ብሎ ልኳቸዋል። በአጭሩ ከታሪኩ የምንማረው አህያይቱ የተባለችው ኦሪት፤ ውርንጭላዋ ደግሞ ወንጌል ናት። በሌላ በኩል የአህያይቱና የውርንጭላዋ ምሳሌ የእስራኤል እና የአሕዛብ ምሳሌ ሲሆን ምሳሌነቱም የተለያዩትን ሁለቱን ወገኖች አንድ ለማድረግ የመጣ መሆኑን ለማስረዳት ነው። ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ **...ለተቀበሉት ሁሉ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው** (ዮሐ. ፩፡፲፪) እንዳለ ጌታም "ፈትታችሁ አምጡልኝ" ማለቱ ሰው ሁሉ ከኃጢአት እስራት የሚፈታበት ጊዜ መድረሱን ሲያስረዳ ነው። ከዚህ በተጨማሪም "ፈትታችሁ አምጡልኝ" ማለቱ የሐዋርያትን ሥልጣነ ክህነትን ያሳያል። ለሐዋርያት የማሰርና የመፍታት ሥልጣን ሰጣቸው ሲል ሥልጣኑ በሐዋርያት እግር የተተኩ ጳጳሳትንና ቀሳውስትን ሁሉ ያጠቃልላል። የተወደዳችሁ ክርስቲያኖች፡- ልንረዳውና ልናጤነው የሚገባ የአምላካችንን ትህትናና ፍቅር ነው። እራሱን ዝቅ አድርጎ በአህያ ላይ የተቀመጠው የሰውን ልጅ ለማክበርና ለመቀደስ ነው። እኛ የእርሱ እውነተኛ ልጆቹ ነን ብለን ደፍረን ልንመሰክር የምንችለው ንስሐ ገብተን ኃጢአታችንን ተናዝዘን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ስንቀበል ነው። ሌላው ላሳስባችሁ የምፈልገው ይኸች **"ጽርሐ አርያም"** የተሰኘችው ጋዜጣ የቤተሰብ መልእክት የያዘች፣ ሁለገብ የሆነችና የሁሉንም ሕይወት የምትዳስስ መስተዋት መሆኗን እንድታውቁ ነው። ሁላችን መልእክቱን አንብበን እንድንጠቀም የልዑል እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ይሁን።

በዓሉን የበረከት የረድኤት በዓል ያድርግልን፤ ሳምንቱን በሰላም በጤና አሳልፎ
ብርሃነ ትንሣኤውን ያሳየን አሜን !!!
መልአከ አርያም ቆሞስ አባ ኃይለሚካኤል ሙላት

## የአዘጋጆች መልዕክት

"ጽርሐ አርያም" የተሰኘው ይኸ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ርእሰ አድባራት ጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እየተዘጋጀ ለምእመናን የሚወጣው ወርኃዊ ጋዜጣ ለመጀመርያ ጊዜ ዛሬ ሚያዝያ ፲፮/፳፻፰ ዓ.ም. (Apr. 24/2016) በሰበካ ጉባኤው አሳሳቢነትና አስተባባሪነት በተዋቀረው የአዘጋጅ ክፍል **የቤተ ክርስቲያናችን ቀኖና (ሥርዓት) ተጠብቆ መጓዝ አለብን በማለት የመጨረሻ ውሳኔያችንን በቁርጠኝነት በገለጽንበት በሁለተኛው ዓመት በዕለተ ሆሣዕና** በእንዲህ ያለ መልኩ ለምእመናን ቀርቧል። ይኸ ወርኃዊ ጋዜጣ ከተለዋዋጭ ዓምዶቹ ባሻገር ዜና ርእሰ አድባራት፣ ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን፣ ነገረ ቅዱሳን፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ይህን ያውቁ ኖሯል? ቅዱሳት መጻሕፍት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት (ጥያቄና መልስ)፣ ወጣቶች እና ሕፃናት (*Amharic and English*)፣ የቤተሰብ ዓምድ፣ የጤና አምድ፣ የወሩ እንግዳ፣ ማስታወቂያ እና ጠቃሚ መረጃዎች የሚሉ ቋሚ ዓምዶች ይኖሩታል። የዚህ ክፍል አዘጋጆች ጋዜጣው የሁላችን መማማሪያ መሆኑን በማመን ሙያዊ እገዛ ለሚያደርጉ እና ከላይ በተዘረዘሩት ዓምዶች ውስጥ የተለያዩ መንፈሳዊ ጽሑፎችን ለሚያቀርቡ ምእመናን የክፍሉን መስፈርት እስካሟሉ ድረስ በሩ ክፍት መሆኑን እናሳውቃለን።

የሕትመት ወጪን በመቀነስ ረገድ ከዚህ ከመጀመርያው እትም በቀር ሌሎቹ ወርኃዊ ጋዜጦች ሁልጊዜ በወሩ መጨረሻ ባለው ሳምንት በድረ-ገጻችን *www.minnesotaselassie.org* ላይ ይወጣሉ። አንባብያን ትምህርቱን ከመከታተል፣ መልእክቶቹን ከማወቅና ጠቃሚ መረጃዎችን ከመረዳት ባሻገር የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በጥያቄና መልስ እንዲሁም በሰንጠረዥ መልኩ ስለሚቀርብ ለልጆቻችሁ ማስተማርያ እንዲሆን ተሳታፊነታችሁ አስፈላጊ ነው እንላለን። ከዚህ በተጨማሪም ወጣቶች እና ሕፃናት በሚለው ዓምዳችን ላይ ሕፃናት የሚሳተፉበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄዎች ስላሉ የጋዜጣችን ተከታታይ እንድትሆኑ በቤተ ክርስቲያናችን ስም እንጋብዛለን።

*በቤተ ክርስቲያናችን ድረ ገጽ ላይ ጋዜጣችንን ለማንበብ፡- http://www.minnesotaselassie.org/newsletter/*

*አስተያየት ለመስጠት ወይም ጥያቄ ካለዎት ኢሜላችን (email) ፡- newsletter@minnesotaselassie.org*

## ማውጫ


| ዝርዝር | ገጽ |
|---|---|
| 1. ፈትታችሁ አምጡልኝ — መልአከ አርያም ቆሞስ አባ ኃይለሚካኤል ሙላት | 1 |
| 2. የአዘጋጆች መልእክት | 1 |
| 3. ትምህርተ ሃይማኖት — መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ስንታየሁ ደምስ | 2 |
| 4. ትምህርት በሠንጠረዥ — አቶ አብርሃም ሰሎሞን | 2 |
| 4. ነገረ ቅዱሳን — መጋቤ ሃይማኖት ቀሲስ አሐዱ አስረስ | 3 |
| 5. ሰሙነ ሕማማት — ሊቀ ብርሃናት ቀሲስ ሄኖክ ያሬድ | 4 |
| 6. የሕፃናት እና ወጣቶች ዓምድ — ወ/ሮ ሰብለወንጌል ደምሴ | 5 |
| 7. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በጥያቄ እና መልስ — ዶ/ር ሰሎሞን ፎሌ | 6 |
| 8. ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን — መ/ኅሩያን ቀሲስ መጽናኛዬ ኃይሌ | 7 |
| 9. ጠቃሚ መረጃዎች — ወ/ት ዘመናይ ዘሪሁን | 8 |


**እዘጋጆች**

ሊቀ ብርሃናት ቀሲስ ሄኖክ ያሬድ
ዶ/ር ሰሎሞን ፎሌ
ወ/ሮ ሰብለወንጌል ደምሴ
ወ/ት ዘመናይ በጋሻው
አቶ አብርሃም ሰሎሞን

**አርታእያን**

መ/አርያም ቆሞስ አባ ኃይለሚካኤል ሙላት
ሊቀ ብርሃናት ቀሲስ ሄኖክ ያሬድ

**ዲዛይን**

አቶ ውብሸት አየለ
ዶ/ር ሰሎሞን ፎሌ

# ትምህርት ሃይማኖት

## እኛም ለአባቶች የተሰጠውን ተስፋ የምስራችን ለእናንተ እንሰብካለን። (ሐዋ. ፲፫፥፴፪)

ይህን ቃል ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ እግር ሥር ቁጭ ብለው የተማሩት ሐዋርያት ተናግረውታል። ጸሐፊው ደግሞ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ነው። በ64 ዓ.ም. አካባቢ እንደጻፈው ይነገራል። መጽሐፉ ሐዋርያት የክርስቶስን ወንጌል ከይሁዳ ወደ ሰማርያ፤ ከሰማርያ ወደ ሶርያ ከዚያም ወደ እስያ ወደ ግሪክና ወደ ሮሜ እንዴት እንዳስፋፉ ያስረዳል። የመጽሐፉ ዓቢይ ነገር የሚያወሳው የሐዋርያትን ሥራ ሲሆን በይበልጥ አጉልቶ የሚናገረው ግን ሐዋርያት በወንጌል ያደረጉትን ተጋድሎና የተጓዙበትን ውጣ ውረድ፣ ለወንጌል የከፈሉትን መሥዋዕትነትና የፈጸሙትን ተአምራት ነው። ከቃሉ መነሻነት እንደምንመለከተው ሦስት ዋና ዋና ነገሮች እናገኛለን፦

**፩) ለአባቶች የተሰጠው ተስፋ**

አባታችን አዳም ከተፈጠረበት ጊዜ አንስቶ በተስፋ እና በደስታ ይኖር ነበር። ይህ ተስፋው ለዘለቄታ እንዳይቆይለት አትብላ የተባለውን ዕፀ በለስን በበላ ሰዓት ተስፋ-ቢስና መንገዱ ሁሉ የጨለማ እና የሁከት ሆኖበታል። ለዚህ ነው ***"ራቁታችውን ሆኑ"*** የሚል የመጽሐፍ ንባብ የምናነበው። አባታችን አዳም ያጣውንና የተሚጠጠበትን የተስፋ ሕይወት ከገነት ከመውጣቱ በፊት ፈጣሪ እንዲህ ብሎ የተስፋ ስንቅን ይዞ እንዲወጣ አድርጎታል።.....**እንተም እናቱን ትቀጠቅጣለህ** (ዘፍ. ፫፥፲፭)። አባታችን አዳም ራቁቱን በነበረበትና አትብላ የተባለውን ዕፀ በለስ በልቶ ከፈጣሪው በተጣላበት ሰዓት ይህን ልዩ የሆነ የተስፋ ቃል ከገነት ይዞ ወጥቷል። ስለሆነም ከገነት ወጥቶና ወድቆ እንደማይቀር ያኔ ከገነት ያባረረው ሰይጣን እናቱን ተመትቶ አዳም ከዘመናት በኋላ ወደ ገነት እንደሚመለስ የተስፋ ስንቅ ሰንቆ ወጥቷል ።

ይኽ ለአዳም ቃል የተገባለት የተስፋ ስንቅ እውን እንደሚሆን እግዚአብሔር በብዙ ምሳሌና ትንቢት ሲያሳይና ሲያናግር ቆይቷል። በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ስለሚሆነው የወደፊት ትንቢት እንደሆነና እንደተደረገ አድርጎ ትንቢት በመናገር የሚታወቀውና ደረቅ አዲስ ኪዳን በመባል የሚታወቀው የኢሳይያስ ትንቢት ዋነኛው ነው። **ድንግል በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች።** (ኢሳ. ፯፥፲፬) ይህ የአዳም የተስፋ ቃል ኪዳን በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚፈጸም ሲያስረዳ በጎቱም ድንግልና ተፀንሶ በጎቱም ድንግልና እንደሚወለድ ተናግሯል። በመቀጠልም የሚወለደው አምላክ **ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ** እንደሆነ በትንቢቱ ተናግሯል። (ኢሳ. ፱፥፯) እንግዲህ ይህ የሚያሳየን ለአዳም የተሰጠው ብቸኛው ተስፋ የዘላለም አባት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ አዳም ያጣውን የልጅነት ጸጋ በሰላም ሲመልስለት እንደሚመጣ ይኽም የማይጨበጥ የማይሆንና የሚዘገይ ተስፋ ሳይሆን እውነት ያለው መሆኑን ያስረዳል ። "አበ ብዙኃን" አብርሃም እንደዚህ የሚል የተስፋ ቃል ተነገሮታል፦.

የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ ። ይህቸን ምድር ለዘርህ እሰጥሃለሁ። (ዘፍ. ፲፪፥፯) ይኽ ቃል ታላቅ ተስፋው ከዘሩ ክርስቶስ ተወልዶ የምድርን ነገድ ሁሉ እንዲባረኩ እንደሚያደርግ ነው። በዚህ ደግሞ ከአብርሃም ዘር በሚወለደው በክርስቶስ መሆኑንም ነው።

**የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ**

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

## ትምህርት በሠንጠረዥ

አሥራ አምስቱን ጥያቄዎች ከላይ ወደ ታች፣ ከታች ወደ ላይ፣ ወደጎን እና ከላይ ወደታች ያሉትን መልሶች ከሰንጠረዡ ላይ በመክበብ መልሱን ይስጡ።

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ብ | ር | ሃ | ም | ና | ኢ | ያ | ኢ | ቅ |
| ት | ቡ | ገ | ና | ት | ና | ኤ | ል | ያ | ድ |
| ዕ | ቅ | ነ | ደ | ቀ | መ | ዘ | ሙ | ሱ | ስ |
| ቢ | ድ | ቢ | ማ | ዝ | ሙ | ካ | ገ | ር | ት |
| ተ | ስ | ዩ | ተ | ቲ | ር | ር | ዳ | ስ | ድ |
| ኛ | ት | ኤ | ሳ | ው | ያ | ያ | መ | ያ | ን |
| ዓ | ኤ | ል | ሙ | ሴ | ስ | ስ | ቆ | ይ | ግ |
| ይ | ል | ሳ | ሙ | ኤ | ል | ድ | ሮ | ሣ | ል |
| ን | ሳ | ዕ | ጣ | ለ | ኤ | ስ | ን | ኢ | ማ |
| ሆ | ቤ | ት | ሳ | ው | ል | ም | ቶ | ዩ | ር |
| አ | ጥ | ፍ | ት | ሬ | ያ | አ | ስ | ቢ | ያ |
| ሆ | ሣ | ዕ | ና | ፈ | ስ | ን | ቀ | ነ | ም |

፩- ስድስተኛው የኢትዮጵያ ቅዱስ ፓትርያርክ

፪- ካህኑ የመጥምቀ መለኮት አባት

፫- የነቢዩ ኤልያስ ደቀ መዝሙር

፬- በቃና ዘገሊላ ያማለደችው እናት

፭- የቅዱስ ጳውሎስ ስም በጌታችን ከመጠራቱ በፊት

፮- በመምሬ አድባር ዛፍ ሥር እግዚአብሔር የተገለጠለት

፯- ስምንተኛው የዐቢይ ጾም ሳምንት

፰- እግዚአብሔርን ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ያየው ነቢይ

፱- ጌታችን ከበለስ ዛፍ ሥር አየሁህ ያለው

፲- በካህኑ ዔሊ ፊት ሲያገለግል የነበረው ብላቴና

፲፩- ጌታችን በዲያብሎስ የተፈተነበት ገዳም

፲፪- የጌታዬ እናት ወደኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆናል ያለች

፲፫- እግዚአብሔር ከሚጠላቸው ፯ ነገሮች አንዱ(መጽ.ምሳሌ)

፲፬- የቅዱስ ጴጥሮስ የቀደመ ስሙ

፲፭- በሙሴ እግር የተተካው

በአቶ አብርሃም ሰሎሞን

# ነገረ ቅዱሳን

ቅዱሳን በገድላቸው በሦስት ይከፈላሉ

ሀ) በአላውያን ነገሥታት ፊት ሳይፈሩ እስከ ደም ጠብታ ድረስ ስለ ክርስቶስ የመሰከሩ ሰማዕታት ናቸው። ለምሳሌ፡-

ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ሰማዕቱ ቅዱስ ቂርቆስ ፣ ቅድስት ኢየሉጣ፣ ቅዱስ መርቆርዮስ እና ሌሎችም።

ለ) በገደል፣ በዱር በዋሻ ሆነው ከጣዕመ ዓለም ተለይተው ክርስቶስ ለሞተለት ለዚህ ዓለም ሲጸልዩ ግርማ ሌሊቱን ድምፀ አራዊቱን ጻብአ አጋንንቱን ታግሠው የሚኖሩ ጻድቃን ናቸው። ለምሳሌ፡-

ጻድቁ ተክለ ሃይማኖት፣ ቅድስት አርሴማ፣ ጻድቁ አቡነ አረጋዊ እና ሌሎችም።

ሐ፡- መጽሐፍ አውጥተው፤ አንቀጽ ጠቅሰው፤ መናፍቃንን ተከራክረው፤ የቤተ ክርስቲያንን ሕልውና ያስከበሩ የቤተ ክርስቲያን ጠበቆች አፖሎጂስቶች/ ተብለው የሚጠሩ ናቸው። ለምሳሌ፡-

ቅዱስ አትናቴዎስ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ፣ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ፣ ቅዱስ ቄርሎስ፣ ቅዱስ ባስልዮስ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ።

እነዚህ ከላይ በግብራቸው የገለጽናቸው ቅዱሳን አክባሪያቸው ባለቤቱ እራሱ አምላክ ነው። ለዚህም ነው ቅዱስ ቃሉ **እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል።** በማለት የገለጸው (፩ቆሮ. ፰፡፲፫) ምክንያቱም የቅድስና ሰጪው እርሱ ነውና:: ከነቢያትም ነቢዩ ኢሳይያስ በምዕራፍ ፶፮፡፲፫ “እግዚአብሔር የቀደሰውን ክቡር ብትለው" በማለት የምናገኘውን በረከት ይገልጻል። በነገረ ቅዱሳን ትምህርታችን ዘወትር ሰዎች ሊያስተውሉት የሚገባ ነገር ቢኖር ለቅዱሳን ክብር የሰጠ እግዚአብሔር ዘወትር የማይጠፋ ስም በቤቱና በቅጥሩ ውስጥ እንዲህ ሲል መስጠቱን ነው፡- **ሰንበቴን ስለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘኝንም ነገር ስለመረጡ ጃንደረቦች ዘወትር የማይጠፋ ከወንዶችና ሴቶች ልጆች ይልቅ የበለጠ ስም በቤቴና በቅጥሬ ዉስጥ እሰጣቸዋለሁ።** ብሎ ቃል ገብቶላቸዋል። (ኢሳ. ፶፮፡፭)

## የቅዱሳን አማላጅነት

ምልጃ በቁሙ ስንፈታው “መለመን፤ ስለሌላው መጸለይ” የሚል ፍቺ ይሰጠናል። አማላጅነት ስንል ደግሞ አድራጊው ያለውን የባለቤትነት ሥልጣን ወይም ችሎታ የተሰጠውን የሚያሳይ ነው። ቅዱሳን የአማላጅነት ጸጋ ተሰጥቷቸዋል፤ ለማማለድም ሥልጣን አላቸው። አማላጅነታቸው ከሰው ወይም ከባለሥልጣን የተሰጠ ሳይሆን ከኃያሉ እግዚአብሔር ነው። ቅዱሳን የተሰጣቸው የማማለድና የመለመን ጸጋ በማንም አለማመን ምክንያት አይነጠቅባቸውም፤ የምልጃ ሥራቸውም የሚቀር አይደለም። ፈርዖን እግዚአብሔርን ሥራውን በሙሴ አማካኝነት በማድረጉ አልተቀበለውም። ምክንያቱም ፈርዖን አለማመኑ ብቻ ሳይሆን እንደርሱ በፈርዖን ቤት ያደገውና የሚያውቀው ሙሴ ከእርሱ ጋር ልዑል ተብሎ በፈርዖን ቤት ሲጠራ ማየት በእርሱ አመለካከት ውስጥ “**ከኔ በምን ይለያል፣ እኔ የማመልከውን ጣዖት አብሮ ሲያመልክ የነበረ ዛሬ እግዚአብሔር የሚለኝ እርሱ ማነው? ባንተ እጅ የምትደረገዋ ተአምር አታስደንቀኝም ምክንያቱም እጅህ ብዙ የፈርዖን ቤት ጥበብና የምትሐት ሥራ ያውቃል**” ብሎ ስለናቀው እግዚአብሔር ተአምራቱን ከእርሱ ጋር ባላደገውና በአይሁዳዊው ዮካብድ ቤት ባደገው አሮን በበትሩ እንዲሠራ አድርጎታል። ሙሴን ፈርዖን መስማት ያቃተው “እንደኔው ነው” በማለትና በማቃለል ነበር። ሆኖም ግን እግዚአብሔርን ባያምን የእግዚአብሔር ሥራ አልተቋረጠም። ዛሬም የማያምኑ እንደኛው ሰው ናቸው በማለት ለሰውነት የተሰጠውን ክብርና እግዚአብሔር በጸጋ በበረከት ታላላቅ ያደረጋቸውን ቅዱሳን አማላጅነት የማይቀበሉ ቢኖሩም አምኖ አማላጅነታቸውን ለጠየቀ ግን የአማላጅነታቸው በረከት ይደርሰዋል፤ ጸጋውም ይበዛለታል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሁለተኛው የቆሮንቶስ መልእክቱ በእኛ የማስታረቅ ቃል አኖረ። (፪ቆሮ. ፭፡፳) ይለናል። **"ወንህነሰ ንተነብል በአምሳለ ክርስቶስ ወይሁበክሙ እግዚአብሔር ፍሥሐ በላዕሌነ"** ይኸም በክርስቶስ ማላጅ አደረገን፤ እንማልዳችኋለን በማለት ገልጾታል። በእንግሊዝኛውም *God were pleading through us, we implore you on Christ's behalf, be reconciled to God.* እነዚህ ሁሉ የምናያቸው መረጃዎች እራሱ ክርስቶስ የማስታረቅንና የማማለድን ሥልጣን ለቅዱሳን መስጠቱን የሚገልጽ ነው።

የቅዱሳን ጸሎት እጅግ ኃይል እንደምታደርግም **"ብዙኀ ትረድእ ለጻድቅ ትክል ወታሰልጥ"** የጻድቅ ሰው ጸሎትዋ በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች። (ያዕ. ፭፡፲፮) በማለት ቅዱስ ያዕቆብ የገለጸው በጸሎት ያለው ዋጋና በረከት የበዛ መሆኑን ለማመልከት ነው። ማንም ከሚጸልየው ጸሎት ይልቅ የጻድቁ ልመና በባለሟልነቱ ኃይል አላትና። ልመናን ማንም ሊለምን እንዲችል የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ነገር ግን ግዳጅ ያላት ግዳጅዋን የምትፈጽም ጸሎት ከእኛ ካለው ንጽሕና ጋርና ለእግዚአብሔር ካለን ቅርበት የሚከናወን ነው። ግብራችን እግዚአብሔርን የማይመስል ሆኖ በሥጋዊ ስሜትና ፍላጎት ታጥረን ሌትና ቀኑን ነፍሳችንን ስለ ሥጋዋ እንጂ አምላክዋን ስለማሰብ እድል ካልሰጠናት ጸሎታችን ለመሰማት ኃይል አይኖራትም። እራሳችንንና ጸጋችንን ማስተዋል ይገባል፤ ደፋር እንዳንሆንም መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

በነቢዩ በኢሳይያስ **መስማትን ትሰማላችሁ አታስተውሉምም፤ ማየትንም ታያላችሁ አትመለከቱምም፤ በዓይናቸው እንዳያዩ፥ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ፥ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፥ ተመልሰውም እንዳይፈወሱ፥ ልባቸውን አደንድን፥ ጆሮአቸውንም አደንቍር፥ ዓይናቸውንም ጨፍን።** (ኢሳ. ፮፡፱-፲) እንደተባለ ዛሬም በብዙዎች ሕይወት ባለማስተዋላቸው ምክንያት እግዚአብሔር ያከበራቸውን ክቡር ብሎ ጠርቶ እግዚአብሔርን ለማመስገን ተቸግረዋል። ቅዱስ ዳዊት ከድፍረት ኃጢአት ጠብቀኝ ያለውን እውነት እናስተውላለን።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተመዘገበው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብቻ በአማላጅነት አሥራ አምስት ሰዎች ተመዝግበዋል። ከዚህ በታች ያሉትን ጥቅሶች በማንበብ ቅዱሳን በመጽሐፍ ቅዱስ ያላቸውን ድርሻና ተሰሚነት ልብ እንበል።


| | | |
|---|---|---|
| ማቴ. ፪፡፳ | ማቴ.፯፡፳፭ | ማቴ. ፰፡፭ |
| ማቴ. ፰፡፳፪ | ማቴ. ፱፡፪ | ማቴ. ፱፡፲፰ |
| ማቴ. ፲፭፡፳፪ | ማቴ. ፲፯፡፲፬ | ማር. ፱፡፲፯ |
| ሉቃ. ፭፡፲፰ | ሉቃ. ፯፡፪ | ሉቃ. ፱፡፴፭ |
| ዮሐ. ፬፡፵፯ | ሐዋ. ፲፮፡፫ | ሐዋ. ፱፡፴፯ |

ቅዱሳን በሕይወተ ሥጋም ሆነ ከሞቱ በኋላ ያማልዳሉ።

መጋቤ ሃይማኖት ቀሲስ አሐዱ አስረስ

## ሰሙነ ሕማማት

በአምላካችን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በተመሠረተችው እና ሐዋርያት ባጸንዋት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተለያዩ ጊዜ የተነሡትና በተለያዩ ጊዜያት ጉባኤ ዘርግተው ሃይማኖታዊ ውሳኔ የደነገጉት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በጸሎተ ሃይማኖት ላይ "**ከዚህ በኋላ በሥጋ ታመመ፣ ሞተ፣ ተቀበረ...**" በማለት ሕማሙንና ሞቶ መቀበሩን ከጸፉልንና ካስተማሩን በመነሣት አባቶቻችን ከሆሣዕና ማግስት ጀምሮ እስከ ትንሣኤ ዋዜማ ያሉትን ቀናት"ሰሙነ ሕማማት" ብለው ሰይመውታል። በመሆኑም እኛም አባቶቻችን በእነዚህ ስድስት ቀናት የጌታችንን ሕማሙን በማሰብ በታላቅ ጸሎት፣ ስግደትና ጾም እንድናሳልፍ መጽሐፍ ጽፈው፣ ጸሎት አዘጋጅተውና ሥርዓት ሠርተው ሰጥተውናል። እያንዳንዱ የዓቢይ ጾም ሳምንት የእራሱ መጠሪያ እንዳለው እነዚህም ስድስት ቀናት የየእራሳቸው የሕማሙና የሞቱ መታሰቢያ ስላላቸው እንደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ክንዋኔአቸውን በአጭሩ እናቀርባለን፦




### ሰኞ፦ በዚህ የመጀመርያው ዕለት

◊ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቢታንያ ወደ ቤተ መቅደስ ማምራቱ፤

◊ ፍሬ አልባ የሆነችውን በለስ መርገሙ (ማቴ. ፳፩ ማር ፲፩)፤

◊ ቤተ መቅደሱን ከገንዘብ ለዋጮች ማንጻቱ፤

◊ በቤተ መቅደስ ማስተማሩና ተአምራት ማድረጉ እንዲሁም በቢታንያ ማደሩ ይነገራል።

### ማክሰኞ፦ በዚህ በሁለተኛው ዕለት

◊ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቢታንያ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዱና የረገማት ቅጠል ከነሥሯ ደርቃ እንዳያት፤

◊ ለሕግ ጠባቂዎችና መምህራን ፈሪሳውያንና የአይሁድን ትምህርት ለተማሩ የጥቂት ሰዱቃውያንን ጥያቄ መመለሱ፤

◊ ስለ ዳግም ምጽአቱና ስለ ቤተ መቅደሱ መፍረስ ማስተማሩ፤

◊ ስለ ወይኑ ቦታና ስለ ሠራተኞቹ፣ (ማቴ. ፳፩) ስለ ንጉሡ ልጅ ሠርግ (ማቴ. ፳፪) ስለ ልባሞቹና ስለ ሰነፎቹ ደናግል በምሳሌ ማስተማሩ፤

◊ በድጋሚ ወደ ቢታንያ ስለ መመለሱ ይነገራል። (ማቴ. ፳፮)

### ረቡዕ፦ በዚህ በሦስተኛው ዕለት

◊ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ሙሉ ቀን በቢታንያ ስለማሳለፉ፤

◊ ኃጢአተኛዋ ሴት መዓዛው የጣፈጠ ሽቱ በጌታችን ላይ ስለማፍሰስዋ (ማቴ. ፳፮) (ይኸቺም ሴት በጌታችን እግር ላይ ዘይት እያፈሰሰች በፀጉሯ ያበሰችው የአልዐዛር እኅት ማርያም አይደለችም) እና

◊ የአስቆሮቱ ይሁዳ በሠላሣ ዲናር ጌታን አሳልፎ ለመስጠት ከአይሁድ ጋር መስማማቱ፤

◊ ካህናተ አይሁድ ሊይዙት መምከራቸው ይነገራል።

### ሐሙስ፦ በዚህ በአራተኛው ዕለት

◊ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ለፋሲካ የሚሆነውን እራት እንዲያዘጋጁ ነግሯቸው ስለማዘጋጀታቸውና የደቀ መዛሙርቱን እግር አጥቦ የምሥጢረ ቁርባንን ሥርዓት መሥራቱ፦ እንጀራንም አንሥቶ አመሰገነ ቆርሶም ሰጣቸውና። ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ። ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው።(ሉቃ. ፳፪:፲፱-፳)

◊ የኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ጸሎት ማድረግ፦ አባት ሆይ፥ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር። (ሉቃ. ፳፪:፵፪) መባሉ ይነገራል።

### አርብ፦ በዚህ በአምስተኛው ዕለት

◊ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳም በበደለ ጊዜ ከሳሽ ዲያብሎስን ***በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።*** (ዘፍ. ፫:፲፭) በማለት የገባለት ቃል መፈጸሙ፤

◊ ስለ ጌታ መያዝ፣ መገረፍ፣ መሰቃየትና መሰቀል ይነገራል። በቤተ ክርስቲያንም ከሰኞ እስከ ሐሙስ ከሚደረገው ስግደት በበለጠ ነገረ መስቀሉን በማሰብ በጸሎትና በስግደት ዕለቱ ይከበራል።

### ቅዳሜ፦ በዚህ በስድስተኛው ዕለት

◊ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሙታን እንደሰበከላቸው **በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፥ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው፤** (፩ጴጥ. ፫:፲፱) እንዲል።

ከዚህ በተጨማሪም በኖኅ ዘመን ስለ ውኃው መጉደል ርግብ የለመለመ ቅጠል ይዛ እንደመጣች የቅዳሜ ስዑር ዕለትም ካህናት "ክርስቶስ በመስቀሉ ሰላምን አደረገ።" በማለት ለሕዝቡ የለመለመ ቄጠማ ያድላሉ። ምክንያቱም በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትም የኃጢአት ባሕር እንዲሁ ተወግዷልና። ይኸ ዕለት ቅዳም ስዑር ይባላል። ትርጓሜውም "የተሻረ" ማለት ነው። ይኸውም ቅዳሜና እሑድ ጾም የማይገባ ሆኖ ሳለ ጌታ በከርሠ መቃብር ስላደረ በአክፍሎት ስለሚጾም ቅዳም ስዑር ይባላል።

**እንበለ ደዌ ወሕማም፤ እንበለ ፃማ ወድካም፤ ያብጽሐነ ያብጽሕከሙ እግዚአብሔር በፍሥሐ ወበሰላም።**

ሊቀ ብርሃናት ቀሲስ ሄኖክ ያሬድ

# የሕፃናት እና ወጣቶች ዓምድ

## ከሕፃናት እና ከሚጠቡ ልጆች አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ

### (መዝ. ፰:፪ )

ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ! እግዚአብሔር እያሉ የሚያመሰግኑ የሰማይ መላእክት በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት የመቆምን ዕድል አግኝተው ምስጋና ገንዘባቸው ሆኖ ሲያመስግኑ ይኖራሉ። ሕፃናትም ለአምላካቸው የሚያቀርቡትን ድንቅ ምስጋና አስመልክቶ ኢየሱስ ክርስቶስ ለካህናት አለቆችና ለጻፎች “ከሕፃናትና ከሚጠቡት አፍ ምስጋናን ለራስህ አዘጋጀህ" የሚለውን ቃል




ከቶ አላነበባችሁምን? እንዳላቸው ተጽፎ እናነባለን። ቤተ ክርስቲያን ለሕፃናት ተገቢውን ሥፍራ ሰጥታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አምላካቸውን ቀርበው እንዲያመሰግኑ በተለየ እንክብካቤ የምትመለከታቸው አስቀድሞ የወደዳቸውና የምስጋና አንደበትን የሰጣቸው እርሱ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በመሆኑ ነው።

ሕፃናት በልዑል እግዚአብሔር ፊት የሚወደዱና እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚፈልገው ዓይነት ልበ ንጹሕ ሆነው በመገኘታቸው ፈሪሳውያን ጌታችንን ሊፈትኑት ጥያቄ ባቀረቡበት ወቅት በሰጣቸው ምላሽ ላይ ***ሕፃናትን ተዉአቸው፥ ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው፤ መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉ ናትና*** (ማቴ. ፲፱:፲፫-፲፭) በማለት ሲናገር እንሰማዋለን። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የጌታችንን አስተምህሮ በመከተል ሕፃናትን እያስተማረችና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተገቢውን እንክብካቤ እያደረገች ዛሬ በደረስንበት ደረጃ ላይ እንድንታይ አስችላናለች።

ዛሬም የታላቁ ደብር የርእሰ አድባራት ጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከመቼውም በበለጠና በተሻለ እንቅስቃሴ ሕፃናቶችንና አዳጊ ወጣቶችን በሳምንት ሁለት ጊዜ ቅዳሜና እሑድ የወንጌል እና የአብነት ትምህርት በማስተማር ሕፃናት ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲወዱና ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲያውቁ ታላቅ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች። በዐውደ ምሕረት ላይ በተለያዩ ዕድሜ ላይ ያሉ ሕፃናት እና ወጣት ልጆቻችን ዝማሬ ለማቅረብ በእግዚአብሔር ፊት በየሳምንቱ ይቆማሉ። የነገዪቱ ቤተ ክርስቲያን ተረካቢዎች የዛሬዋ ሕፃናት ሊሆኑ የሚችሉት ገና ከአሁኑ በዚህ ዕድሜያቸው በፈሪሐ እግዚአብሔር ታንጸው ቤተ ክርስቲያንን ማወቅ ሲችሉ ብቻ ነው። የተጀመረው ትምህርት ሳይቋረጥና እየታየ ያለው እንቅስቃሴ ሳይዳከም መራመድ ከቻልን እግዚአብሔር የወደዳቸውንና መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ምሳሌ ያደረጋቸውን ሕፃናት ከአሁኑ በበለጠ በመንከባከብ ማንነታቸውን ልናሳውቃቸው እንችላለን። ሕፃናት የነገሯቸውን አይረሱምና ቶሎ ለመማርም አእምሯቸው ፈጣን ነውና ጊዜ በማጥፋት መልካሙን ሁሉ ልናስተምራቸው የሚገባን በአሁኑ ሰዓት ነው። ጠቢቡ ሰሎሞን ለሕፃናት ትምህርት የሚያስፈልገው በጊዜ መሆኑን ሲያስረዳ ፡- ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም። (ምሳሌ ፳፪:፮) ይለናል።

### PUZZLE FOR CHILDREN

**Rules:-** Answer each of the 10 questions below, and locate the answer vertically or horizontally in the grid.

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| S | E | L | A | S | S | I | E | D | M |
| D | M | O | S | E | S | O | J | E | A |
| E | L | I | J | A | H | F | U | G | R |
| J | O | H | N | D | A | Y | D | Y | Y |
| S | E | L | F | O | R | N | A | P | B |
| G | O | L | I | A | T | H | H | T | A |
| B | E | T | H | L | E | H | E | M | S |
| Z | A | C | C | H | A | E | U | S | H |

**Questions**

1) Who fought against King David?
2) What was the name of the short man who climbed a tree so that he can see Jesus Christ?
3) Who received the ten commandments from God?
4) Who has ascended into heaven ?
5) Who is The Mother of Jesus Christ?
6) Where was Jesus Christ born?
7) Who baptized Jesus Christ?
8) Who among the disciples/apostles had betrayed Jesus Christ?
9) What was the country the Mother of Christ fled to so as to escape from King Herod?
10) What is the name of our Church?

በወ/ሮ ሰብለወንጌል ደምሴ

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በጥያቄ እና መልስ

**ከተሰጡት ምርጫዎች ትክክለኛ የሆነውን ይምረጡ።**

**፩. ስለ ጾም ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?**

ሀ) ጾም የጸሎት እናት የአርምሞ እኅት የዕንባ ምንጭና የመልካም ገድል ሁሉ ጥንተ መሠረት የሆነች የፅድቅ በር ናት፤

ለ) ጾም ፈቃደ አምላክ የምንፈጽምበት፣ ኃጢአታችንን ለማስተስረይ ደካማ ሥጋችንን ለነባቢት ነፍስ የምናስገዛበት ነው፤

ሐ) የዲያብሎስን ኃይል ድል መንሻ የመንግሥተ ሰማያት መውረሻ የሚሆን የሰው ልጆች ብርቱ ጥሩር ነው፤

መ) የምግብ ለውጥ ለማድረግ እና ሁልጊዜ ሥጋ መብላት ጤናችንን እንዳይጎዳ በማሰብ የምንፈጽመው ሥርዓት ነው።

**፪. በዘመነ አበው፣ በዘመነ ኦሪት፣ በዘመነ ነቢያትና በዘመነ ሐዋርያት በመጾም ትልቅ በረከት ስላገኙ ሰዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ!**

ሀ) ክቡደ መዝራዕት ሊቀ ነቢያት ሙሴ በእግዚአብሔር ጣት ዓሥርቱ ቃላተ ኦሪት የተጻፈባቸውን ሁለት ጽላቶች ለመቀበል የበቃው ፵ ቀናት በመጾም ነው፤

ለ) ነቢዩ ኤልያስ ሞት ሳይቀምስ ወደ ብሔረ ሕያዋን በእሳት ሠረገላ ለማረግ የበቃው ፵ ቀናት ከጾመና ከጸለየ በኋላ ነው፤

ሐ) ነቢዩ ዳንኤል የእግዚአብሔር መልአክ የተገለጸለት ሃያ-አንድ ቀን ጾሞ ከጸለየ በኋላ ነው፤

መ) ሁሉም ልክ ነው።

**፫. በጾማችን ወራት ሊኖረን የሚገቡ ምግባሮች የትኞቹ ናቸው?**

ሀ) የሠራነውን ኃጢአት በማስታወስ ራሳችንን ዝቅ አድርገን በተሰበረ መንፈስ እና በዕንባ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ፤

ለ) ወደ ነፍስ አባታችን ቀርበን ንስሐችንን በማቅረብ እና እርስ በእርሳችንም ይቅር መባባል፤

ሐ) የታመሙ እና የታሰሩትን በመጎብኘት፣ እንዲሁም ለድኆችና ለተጨነቁት ካለን መብልና ሀብት ማካፈል፤

መ) ሁሉም ልክ ነው።

**፬. ዓብይ ጾምን ለምን እንጾማለን?**

ሀ) ሙሴ በሲና ተራራ ፵ ቀንና ፵አርባ ሌሊት እንደቆየ ለማስታወስ፤

ለ) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት በመጾም ለእኛ ትልቅ ምሳሌ ለመሆን የጾመው ጾም በመሆኑ፤

ሐ) ኤልያስ እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ድረስ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት መሄዱን ለማስታወስ፤

መ) ዔሊ በእስራኤል ላይ ፈራጅ የነበረበትን ፵ ዓመታት ለማስታወስ፤

ሠ) ሁሉም ልክ ነው።

**፭. ለዓብይ ጾማችን መነሻ የሆነንን ምክንያት የምናገኝበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የትኛው ነው?**

ሀ) ማቴዎስ ፬:፩-፪ ለ) ማርቆስ ፩፥፩-፪-፲፫

ሐ) ሉቃስ ፬፥፩-፪ መ) ሁሉም ልክ ነው።




**፮. የጾማችን የመጀመሪያ ሣምንት ምን ይባላል?**

ሀ) መጻጉዕ ለ) ምኩራብ ሐ) ዘወረደ መ) ሆሣዕና

**፯. የጾማችን ስምንተኛ ሣምንት ምን ይባላል?**

ሀ) መጻጉዕ ለ) ምኵራብ ሐ) ዘወረደ መ) ሆሣዕና

**፰. ጌታችን ዓብይ ጾምን አርባ ቀንና አርባ ሌሊት እንደጾመው ስናውቅ እኛ ግን ለምን 55 ቀናት እንጾማለን?**

ሀ) የአቆጣጠር ስሕተት ነው፤

ለ) በጾማችን ወቅት ያሉት ሰባት ረቡዕ እና ስምንት ዓርቦች ስለማይቆጠሩ፤

ሐ) የመጀመርያው ሳምንት ጾመ ሕርቃል፤ የመጨረሻው ሳምንት ደግሞ ሰሙነ ሕማማት ተብሎ ስለሚጾም ነዉ።

መ) ለምን እንደሆነ አይታወቅም።

**፱. በመጽሐፍ ቅዱሳችን እንደተገለጸው ከጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ፵ ቀን እና ፵ ሌሊት የጾሙ ሁለት ሰዎች እነማን ናቸው?**

ሀ) ሙሴ እና ኤልያስ፤ ለ) ሙሴ እና ዮሴፍ፤

ሐ) ዮሴፍ እና ኤልያስ፤ መ) ዳንኤል እና ኤልያስ፤

**፲. የዐቢይ ጾማችን ሰባተኛ ሣምንት በስሙ የተሠየመለት ኒቆዲሞስን አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው፤**

ሀ) ከፈሪሳውያን ወገን የሆነ ነገር ግን ጌታችንን እስከ መጨረሻ የተከተለ ከ፲፪ቱ ሐዋርያት አንዱ ነው፤

ለ) ፈሪሳዊ እና በሮማውያን የተሾመ የአይሁድ አለቃ ባለ ሥልጣን የነበረ ሰው ነው፤

ሐ) አለቅነትን ከመምህርነት ዕውቀትን ከትህትና ምሁርነትን ከደፋርነት አስተባብሮ የያዘ የጌታችን የምሽት ተማሪ የነበረ ሰው ነው፤

መ) የክርስቶስን ሥጋ ከአለቆች ለምኖ የገነዘ እና በአዲስ መቃብርም ያሳረፈ ሰው ነው።

በዶ/ር ሰሎሞን ፎሌ

ከገጽ 2 የዞረ .......ትምህርተ ሃይማኖት

(ማቴ፩፡፩) እንደተባለ። “እንግዲህ አብርሃም በእግዚአብሔር አመነና ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት። እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደሆኑ አወቁ። መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንዲያጸድቅ አስቀድሞ አይቶ “በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ” ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ። እንግዲህ እግዚአብሔር የተስፋው ብርሃን በአዳም እና በልጅ ልጆቹ አኑሮ አዳምም በተስፋ ወደወጣበት ገነት እንደሚመለስ ሲጠባበቅ ኖሯል። በዓበይት ነብያትና በደቂቀ ነብያት ሲናገር እና ሲያጽናና ቆይቷል። **ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን ።** (ዕብ. ፩፡፩)

**፪) የምስራችን እንሰብካለን**

**ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከና እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ።** (ገላ. ፬፡፬) ለአበው ተሰጥቶ የነበረው ተስፋ እሙን እንደሆነ የተረጋገጠበት የመጨረሻው መንገድ የምሥራች ተብሷል። ይኽም የሐዲስ ኪዳን ውልና ስምምነት ሊፈጽምለት በመጣው በድንግል ማርያም ልጅ ነው። **በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ።** (ኢሳ.፱፡፩) የሐዲስ ኪዳን የመጀመሪያውን የምሥራች በማድመጥ የተመረጠችውና የታደለችው ለድኅነት ምክንያት የሆነችው ድንግል ማርያምን በሚያስደንቅና በሚያስገርም ሁኔታ ብሥራታዊ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል እንዲህ በማለት አበሠራት፡- **ጸጋን የሞላብሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ከአንቺም የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው።** (ሉቃ. ፩፡፳፰-፴፪)

በቀዳማዊ አዳም የራቀው ሰላምና የአንዣበበው የሞት ጥላ ጽድቅ ርቆ ኃጢአትና ርኩሰት በዝቶ በፍርሃትና በኀዘን በሰቆቃው በዲያብሎስ ቁራኝነት ተይዞ ለአምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን የተኖረበት ታሪክ ተቀይሮ የደስታ ብሥራት ተሰማ። ያ የፍዳ ዘመን ተሽሮ አዲስ ዘመን የምሕረት ዘመን ቀረበ። “አዲስ ዜና፣ አዲስ ብሥራት፣ የምሥራች ተሰማ የምሕረት ዓመት ቀረበ” ብሎ አበሠራት። ከዚያም ጌታ የመወለጃው ቀን በደረሰበት ዕለት አሁንም ታላቁን ምሥራች ኖሎት እረኞች አደመጡ። ከብቶቻቸውን እየጠበቁ ባለበት ሰዓት **ዛሬ በዳዊት ከተማ ለሕዝብ ሁሉ የሚሆን ደስታ ተወልዶላችኋል** (ሉቃ. ፪፡፲፩) ተባለ። የሕዝቡ ሁሉ ደስታ በጌታችን መወለድ ሆነ፤ አረጋዊ ስምኦንም እንዲህ አለ፡- ዓይኖቼ ማዳንህን አይተዋልና ባርያህን በሰላም አሰናብተኝ። (ሉቃ. ፪፡ ፳፱-፴)

(ይቀጥላል)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለመስቀሉ ክቡር

መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ስንታየሁ ደምስ (BTH)

# ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን

በአብ ስም አምኜ አብን ወላዲና አሥራጺ ብዬ፤ በወልድ ስም አምኜ ወልድን ተወላዲ ብዬ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምኜ መንፈስ ቅዱስን ሠራጺ ብዬ ምንም ለአጠይቆ አካላት ሦስት ብል በመለኮት በሥልጣን በአምላክነት አንድ አምላክ ብዬ አምኜ ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስና ከሊቃውንተ



ቤተ ክርስቲያን ያገኘሁትን መጻፍ እጀምራለሁ። አምላካችን እግዚአብሔር ለአባቶቻችን ምሥጢሩን እንደገለጸ ለእኛም ይግለጽልን አሜን።

"በዓመት በዓመት በየወራቱ ይኽቺን ሥርዓት ጠብቃት"(ዘጸ. ፲፫፡፲)። ይኽንን ቃል የምናገኘው እስራኤል ከግብፅ የመውጣታቸው ዜና በተጻፈበት መጽሐፍ ነው። ሥርዓትንም ሠርቶ የሰጣቸው በባርነት ሳሉ ሳይሆን ወደ ነፃነት ምድር በመሄድ ላይ ሳሉ ነው። አምላካችን እግዚአብሔር ያዘጋጀልንን መንግሥቱን ያወርሰን ዘንድ ሲወድ የምንመራበትን መመሪያ የምንሠራውንም ሥራ መቼ እና እንዴት ማከናወን እንደሚገባን ሊያሳውቀን ሥርዓትን ሠራልን። የሠራልንን ሥርዓት ደግሞ ዘወትር ልንፈጽመው እንጂ ጊዜና ሁኔታ እየጠበቅን ሥርዓቱን እንዳንተውና እንዳናቃልል በየወራቱና በየዓመታቱ መጠበቅ እንደሚገባን በአጽንዖት ተናገረ። ሥርዓትን ለመጠበቅ ግን መጀመርያ "ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን" ምን እንደሆነ ማን እንደሠራውና ጥቅሙን ማወቅና መረዳት ይበጃል። ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ከማየታችን በፊት ግን ለሁላችንም ግልጽ ሊሆንልን የሚገባው ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ቃል ትርጉምና ምንነት ነው። ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ሦስት ትርጉም እንዳለው የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይገልጹታል፡-

፩) የክርስቲያኖች አንድነት ወይም ስብስብ (ዕብ. ፲፱፡፩)

፪) የክርስቲያን ሰውነት (፪ ቆሮ. ፮፡፲፮፤ ሐዋ. ፲፩፡፳፮)

፫) ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን (ሉቃ. ፩፡፳፩፤ኢሳ.፵፬፡፳፫)

ከእነዚህ ከሦስቱ የመጀመርያውን ወስደን ምን ማለት እንደሆነ እንመለከታለን። በክርስቶስ ኢየሱስ ጌትነት ፍጹም የባሕርይ አምላክነትና ፍጹም ሰውነት የሚያምኑና የሚታመኑ ሁሉ ክርስቲያን ወይም ክርስቶሳውያን ይባላሉ። ስለዚህም መላእክት ቀርበው ያገለግሉት ነበረ።

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ከገጽ 7 የዞረ .......ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን

(ማቴ. ፬፥፲፩) ስለዚህ መላእክት ከክርስቲያን ማኅበር ናቸው ማለት ነው። ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። (ኢሣ. ፱፥፮) ነቢያትም ከዚሁ ሕብረት ናቸው። ...ቅዱስ መጽሐፋችንም "ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ።" (ሐዋ. ፲፩፥፳፯) ይለናል። ስለዚህ በሥጋም በነፍስም በመንፈስም ያሉ የክርስቶስ አማኞችና አገልጋዮች ሕብረት አንድነት ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ይጠራል።

የቤተ ክርስቲያን ትርጉም እንዲህ ከሆነ ሥርዓት ምንድር ነው? ሥርዓት ማለት ሠርዓ ሠራ ካለው የግዕዝ ቃል የወጣ ሲሆን ሥርዓት አሠራር አፈጻጸም መመሪያ ማለት ነው። በመሆኑም ሥርዓት የቤተ ክርስቲያንን ሕግጋት የምንፈጽምበት (የምንሠራበት) መመሪያ ማለት ነው። አምላክህ እግዚአብሔር ይህን ሥርዓትና ፍርድ ታደርግ ዘንድ ዛሬ አዝዞሃል፤ አንተም በፍጹም ልብህና በፍጹም ነፍስህ ጠብቀው፥ አድርገውም። (ዘዳ. ፳፮፥፲፮) ስለዚህ ሥርዓት ማለት ልንጠብቀውና ልንፈጽመው የሚገባና በሆነውም ባልሆነውም የሚቀየርና ሲመች የሚፈጽሙት ሳይመች የማይፈጽሙት አይደለም። ሥርዓት ማለት በመላእክት ተራዳኢነት በቅዱሳን ጸሎት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በቅዱሳን አባቶች (በቅዱስ ሲኖዶስ) የሚሠራ እንጂ እንደ ዓለማውያን መመሪያ በዚህ ይስተካከል ይኼ ይቀነስ ወይም ይጨመር የማይባል ነው። (፪ ጴጥ. ፩-፳) ስለዚህ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን አባቶች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የሚሠሩትና ዘመናትን ተመልክተው የሚጨመረውን እየጨመሩ የሚሻሻለውን እያሻሻሉ የሚቀጥል እንጂ የሚቀነስ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የለም። ማንም የራበው ቢኖር ለፍርድ እንዳትሰበሰቡ በቤቱ ይብላ። የቀረውንም ነገር በመጣሁ ጊዜ እደነግጋለሁ። (፩ ቆሮ. ፲፩፥፴፬) ይኸንን ያህል ስለ ሥርዓት ካልን በቤተ ክርስቲያን ስለሚፈጸሙ ሥርዓቶች ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በሚቀጥለው ጽሑፍ እንገናኛለን። አነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን በአንድነት በሦስትነት ለሚመሰገን ለሥላሴ ክብር ምስጋና ይሁን አሜን።

መጋቤ ኅሩያን ቀሲስ መጽናኛዬ ኃይሌ

# በቤተ ክርስቲያናችን የሚሰጡ አገልግሎቶች

**ቅዳሴ፣ ማሕሌት፣ ኪዳን፣ ምህላ እና ንግሥ**

- ◊ ዓመቱን በሙሉ ኪዳን ይደርሳል (6:00 A.M)
- ◊ ዘወትር እሑድ ቅዳሴ ይቀደሳል
- ◊ በሥላሴ፣ በመድኃኔዓለም፣ በማርያም፣ በሚካኤል እና በዮሐንስ ወርኃዊ በዓላት ይቀደሳል (የክርስትና ማንሳት አገልግሎት ይሰጣል)
- ◊ ጥርና ሐምሌ ሥላሴ፣ ጥቅምት እና መጋቢት መድኃኔዓለም፣ ኅዳር እና ሰኔ ሚካኤል፣ ሰኔና መስከረም ዮሐንስ ይነግሣል
- ◊ በጾመ ፍልሰታ የሱባኤ ወቅት ሰዓታት ይቆማል፣ ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ይተረጎማል፣ ቅዳሴ እና የሰርክ ጸሎት ይደርሳል
- ◊ በአዲስ ዓመት (በዘመን መለወጫ)፣ በልደት በትንሣኤ እና ቤተ ክርስቲያናችን ባሏት ተጨማሪ ዐበይት በዓላት የተለያዩ መርሐ-ግብሮች ይከናወናሉ።
- ◊ በሰሞነ ሕማማት ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ሙሉ አገልግሎት ይሰጣል

**ስብከተ ወንጌል እና መንፈሳዊ ትምህርት**

- ◊ ዘወትር አርብ ስብከተ ወንጌል ይሰጣል
- ◊ ዘወትር ቅዳሜ መላ ምእመናንን የሚያሳትፍ የሰንበት ትምህርት ቤት መርሐ-ግብር ይደረጋል
- ◊ ዘወትር ቅዳሜ የአብነት ትምህርት እና መሠረታዊ የአማርኛ ቋንቋ ለወጣቶችና ለታዳጊ ሕፃናት ይሰጣል
- ◊ ዘወትር እሑድ ሃይማኖታዊና የሥነ-ምግባር ትምህርት ለሕፃናት እና ለወጣቶች ይሰጣል

**ዕድር**

- ◊ የቤተ ክርስቲያናችን አባላት የሆኑ ብቻ በአባልነት ተመዝግበው በኀዘናቸው ጊዜ መርጃ እንዲሆናቸው ታስቦ የተቋቋመው ዕድር ለአባላት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

**ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣ ለኮሌጅ እና ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች**

- ◊ ዘወትር ቅዳሜ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣ በኮሌጅ እና ዩኒቨርስቲ የቀለም (ዘመናዊ) ትምህርት በመከታተል ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ለሚያነሱት ጥያቄዎች በሙሉ፤ በተለይም የከበዳቸውን እና የተለያዩ የትምህርት ተቋማትን አስመልክቶ ጥያቄ ቢኖራቸው የምክር እና የትምህርት አገልግሎት (*mentoring & tutoring programs*) ይሰጣል።

## ጠቃሚ መረጃዎች፡

- ◊ በአዲሱ የኦባማ ሕግ መሠረት ማንኛውም ነዋሪ የጤና ኢንሹራንስ (*Health Insurance*) ሊኖረው ይገባል። በመሆኑም አሠሪዎች ለሠራተኞች በዓመቱ መጨረሻ 1095C ወይም 1094 C ፎርም ይልካሉ። ያም ፎርም አሠሪው ለሠራተኛው በቂ ኢንሹራንስ እንዲኖረው ማድረጉንና ሠራተኛውም ምን ያህል እንደተጠቀመ ለIRS ሪፖርት ያደርግበታል።
- ◊ በቀረበው ሪፖርት ላይ ሠራተኛው ሙሉ ዓመት የኢንሹራንስ ተጠቃሚ መሆን ሲገባው በተለያዩ ምክንያቶች የግማሽ ዓመት ብቻ ኢንሹራንስ ካስገባ የዓመቱ ተመላሽ ታክስ ላይ ቅጣት ይኖረዋል።
- ◊ ኦባማ ኬር ኢንሹራንስ (*Obamacare*) በትንሹ $9.00 በሳምንት በመክፈል ማግኘት ይቻላል። ይህም ክፍያ እንደ ገቢዎ መጠን ይወሰናል። በስልክ ቁጥር **1-800-909-0428** ቢደውሉ የመጠየቂያ ፎርሙን ማግኘት ይችላሉ።
- ◊ ከኢሚግሬሽን ቢሮ (*US Citizenship and Immigration office* ) የነዋሪነት መታወቂያ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ጥያቄ ቢኖርዎ በስልክ ቁጥር **1-800-375-5283** በመደወል ማነጋገር ይችላሉ።
- ◊ አፓርትመንት የሚፈልግልዎት ካምፓኒ ቢያስፈልግዎ በስልክ ቁጥር **1-888-658-7368** በመደወል ማነጋገር ይችላሉ።

በወ/ት ዘመናይ ዘሪሁን